ASYLEE OUTREACH PROJECT

የHIAS የጥገኞች ስምሪት ፕሮጀክት

HIAS

# የጥገኝነት ፍቃድ አግኝተዋል?

## ከሆነ የሚከተሉትን ለማድረግ ሊፈልጉ ይችላሉ:

### 1. ለጥቅማ ጥቅሞች ማመልከት

እንደ ጥገኝነት ጠያቂነትዎ የጤና መድን ዋስትናን፣ የስራ ፍለጋ እርዳታን፣ የእንግሊዝኛ ክፍለ ጊዜን እና ሌሎችንም ጨምሮ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ብቁ ሊሆኑ ይችላሉ። ለእነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች ማመልከትና ማግኘት በጥገኝነት ደረጃዎ ላይ ተጽእኖ አይፈጥርም። ጥገኝነት ከሚያገኙበት ቀን በኋላ ለእነዚህ ጥቅማ ጥቅሞች ለማመልከት ያሉዎ ውሱን ጊዜ ነው። የተለያዩ ድርጅት ለጥገኞች የተለያዩ ጥቅማ ጥቅሞችን ያቀርባሉ። ያሉት ሜሪላንድ ውስጥ ከሆነ በቅርብዎ በሚገኝ ቢሮ ቀጠሮ ለማስያዝ ወይም ተጨማሪ ለማወቅ እባክዎ የጥገኞች ስምሪት ፕሮጀክትን በ፡ (240) 284-3306 ወይም asyleeoutreach@hias.org ያነጋግሩ። ያሉት ሌላ ግዛት ውስጥ ከሆነ በቅርብዎ የሚገኝ የመልሶ ሰፈራ ድርጅትን ለማነጋገር www.acf.hhs.gov/orr/map/find-resources-and-contacts-your-state ይግቡ።

### 2. ተጨማሪ ሰነዶችን ማግኘት

በፍጥነት ለየትኛውም የማህበራዊ ዋስትና ቢሮ ያልተገደበ የማህበራዊ ዋስትና ካርድ ለማግኘት ሊያመለክቱ ይችላሉ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.ssa.govን ይጎብኙ ወይም በስልክ ቁጥር 1-800-772-1213 ይደውሉ። በተጨማሪም ምንም እንኳን በጥገኝነት ደረጃዎ እስከቀጠሉ ድረስ ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ መስራት የሚፈቀድልዎ ቢሆንም የስራ ቅጥር ፍቃድ ሰነድ (EAD) በተጨማሪም የስራ ፍቃድ ተብሎ የሚጠራውን ለማግኘት ሊያመለክቱ ይችላሉ። ተጨማሪ ለማወቅ www.uscis.gov/i-765ን ይጎብኙ። በመጨረሻም የተወሰኑ ጥቅማ ጥቅሞችን ለማግኘት ቅጽ I-94 ሊያስፈልግዎ ይችላል። አንዱን የሚያገኙበት ቀጠሮ ለማስያዝ ለUSCIS (800-375-5283) ይደውሉ፣ ጥገኝነት ማግኘትዎን ይግለጹላቸውና የInfoPass ቀጠሮ እንዲይዙልዎ ይጠይቋቸው።

### 3. ከተቻለ ለቤተሰብዎ አባላት ጥገኝነት ለማግኘት መጠበቅ

ለትዳር ጓደኛዎና ለልጆችዎ የአምጪ ጥገኝነት ደረጃ ሊጠይቁ ይችላሉ። ጋብቻ የፈጸሙት ጥገኝነት ካገኙበት ቀን በፊት መሆን አለበት እንዲሁም የጥገኝነት ማመልከቻ በሚያቀርቡበት ወቅት ልጆችዎ ዕድሜያቸው ከ21 ዓመት በታች መሆን አለበት። የጥገኝነት ፍቃድ ከሚያገኙበት ቀን ጀምሮ ለቤተሰብዎ አባላት በጥገኝነት ከእርስዎ ጋር እንዲቀላቀሉ የሚያመለክቱበት የሁለት ዓመት ጊዜ አሉዎ። ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት www.uscis.gov/i-730 ን ይቀላቀሉ።

### 4. ለህጋዊ ቋሚ ነዋሪነት ማመልከት

ጥገኝነት ከሚያገኙበት ቀን ቀጥሎ ለአንድ አመት ያክል ዩናይትድ ስቴትስ ውስጥ በአካል ከቆዩ ለህጋዊ ቋሚ ነዋሪነት (ግሪን ካርድ) ሊያመለክቱ ይችላሉ። በግሪን ካርድዎ ላይ የተጠቀሰው ነዋሪነት ከሚጀምርበት ቀን ከአምስት ዓመት በኋላ ለዩ.ኤስ ዜግነት ሊያመለክቱ ይችላሉ። ተጨማሪ ለማወቅ የስደተኞች ጠበቃ ያነጋግሩ ወይም www.uscis.gov/i-485ን ይጎብኙ።

ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት **ASYLEEOUTREACH.ORG/EVENTS**ን ይጎብኙ።
በቀጣዩ የኦንላይን ብሔራዊ የጥገኞች ጥቅማ ጥቅሞች ገለጻ ላይ ለመሳተፍ
ፌስቡክ/Facebook ላይ በ @asyleeoutreach ይከተሉን።